UK Health Security Agency

# ስለ ቱበርክሎሲስ (ቲ ቢ)

## ቲቢ አብዛኛውን ጊዜ ሳንባዎቻችንን የሚያጠቃ በሽታ ነው። በባክቴሪያ ይነሳል። አደገኛ ሊሆን ይችላል ግን በአንቲባዮቲክስ መታከም የሚችል ነው።

### በ ቲቢ እንዴት መያዝ እንደሚቻል

የቲቢ ምልክት ያለበት አንድ ሰው ሲያስል ወይ ሲያስነጥስ፡ ትንንሽ የባክቴሪያ ነጠብጣቦችን ወደ አየር ይበትናል። በ ቲቢ መያዝ አስቸጋሪ ነው። አስቀድሞ ከተጠቃ ሰው ጋር የቅርብ እና ቀጣይነት ያለው ንክኪ ማድረግ እና የተበከለውን አየር መተንፈስ ያስፈልጋል። 2 ዓይነት ቲቢዎች አሉ፡ ንቁ እና የተኛ ይባላሉ።

### ንቁ ቲቢ

ይህ ማለት ባክቴሪያዎቹ አካልዎ ውስጥ በንቃት [እየሰሩ] ይገኛሉ ማለት ነው። እርስዎ፡

- የህመም ምልክት አለብዎት
- በሽታውን ሊያስተላልፉ ይችላሉ
- ህመም ይሰማዎታል

### የንቁ ቲቢ ምልክቶች

የሚከተሉት ካሉብዎት ሃኪም (ጂፒ) ያነጋግሩ፡

- የማይድን ወይ የማይሻል ሳል
- ደም የተቀላቀለበት አክታ ሲስሉ ከቄዩ
- ትኩሳት ወይም የሌሊት ላብ
- የምግብ ፍላጎት አለመኖር ወይም ክብደት መቀነስ
- ከፍተኛ ድካም

### የተኛው ቲቢ

ይህ ማለት ባክቴሪያዎቹ ሰውነትዎ ውስጥ በንቃት እየሰሩ አይደለም። እርስዎ፡

- የህመም ምልክት የለብዎትም
- በሽታውን ወደ ሌላ ማስተላለፍ አይችሉም

## ቲቢ መታከም የሚችል ነው

ዩኬ ውስጥ ቲቢ ከያዝዎ፡ የነጻ ምርመራ እና ህክምና ያገኛሉ።

## የ ቲቢ ምርመራ

ምንም የህመም ምልክት ባይኖርብዎትም መመርመር ይችላሉ።

ዶክተር ቲቢ እንዳለብዎ ለማወቅ አንድ ወይም የተዛመዱ ምርመራዎችን ሊያካሂድ ይችላል። የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ፡

- የደረት ላይ ራጅ
- የቆዳ ምርመራ
- የደም ምርመራ
- የንፋጭ (አክታ) ናሙና

## በቲቢ የሚያዘው ማን ነው

ማንኛውም ሰው ቲቢ ሊያዝ ይችላል ግን እርስዎ የሚከተሉትን ካደረጉ የበለጠ የመያዝ ዕድል አለዎት፡

- ንቁ ቲቢ ካለበት ሰው ጋር ብዙ ጊዜ የሚያሳልፉ ከሆነ
- ቲቢ በበለጠ የተለመደበት ሀገር ከኖሩ
- የተዳከመ በሽታ የመከላከል አቅም ካለዎት
- በጣም በተጨናነቀ ወይ ጤናማ ባልሆነ ሁኔታ ውስጥ ከኖሩ
- በየጊዜው የሚያጨሱ፣ የሚጠጡ ወይም አደንዛዥ ዕጽ ሚወስዱ ከሆነ
- ከዚህ በፊት ቲቢ ከነበረብዎ እና በሚገባ ያልታከሙ ከሆነ

## የቲቢ ክትባት

የቲቢ ክትባት አለ። ቢሲጂ ተብሎ ይጠራል። ቢሲጂ፡ የኤን ኤች ኤስ ክትባት አንዱ አካል በመሆን በየጊዜው አይሰጥም ምክንያቱም ከፍተና ስጋት ውስጥ ላሉ ሰዎ ብቻ ነው የሚመከረው። ስለ ክትባት ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የ ኤን ኤች ኤስ ድረ-ገጽንnhs.uk/vaccinations/bcg-vaccine-for-tuberculosis-tb/ ይጎብኙ።

## ስለ ቲቢ የበለጠ ይወቁ

በ7 ቋንቋዎች የተዘጋጀውን እና ስለ የተኛው ቲቢ የሚገልጸውን የመረጃ ቪድዮ ይመልከቱ። ይህን ይፈልጉ @TheTruthAboutTB።

ስለ ቲቢ የበለጠ መርጃ ለማግኘት የኤን ኤች ኤስ ድረ-ገጽን ይጎብኙ ወይ ኪው አር ኰዱን ስካን ያድርጉ nhs.uk/conditions/tuberculosis-tb/።

**የ ዩኬ ጤና ጥበቃ ድርጅት**
**ዝግጁነት፣ መከላከል እና ለጤና ስጋቶች ምላሽ መስጠት፣**
**ህይወት ማዳን እና መተዳደሪያን መከላከል።**